707/2013

# የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር

## የሴክተር ተቋማት ዕቅድ አፈጻጸም ምዘናና ግብረ-መልስ

መመሪያ ቁጥር 707/2013

ሰኔ 2004 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

## መ ግ ቢ ያ

የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር የተጣለበትን ዘርፉን የመምራትና የማስተባበር ድርሻውን በመወጣት ልማትን ለማፋጠን፣ መልካም አስተዳደርን ለማስፈንና ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመገንባት የሚያስችሉ የተለያዩ ስትራቴጂያዊ ጉዳዮችን በመለየት ፖሊሲዎችን፣ ፕሮግራሞችን እና ፕሮጀክቶችን በመቅረጽ በመተግበር ላይ ይገኛል፡፡ የስትራቴጂያዊ ጉዳዮችን አፈጻጸም ውጤታማነት እና ቀጣይነት ለማረጋገጥ በሁሉም ደረጃ የሚገኙ የሴክተር ተቋማትን አፈጻጸም ደረጃ በመለየት እውቅና መስጠት ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም በፌደራል፣ በክልሎች እና በአዲስ አበባና በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮች በሚገኙ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ዘርፍ ተቋማት የእቅድ አፈጻጸም በየወቅቱ መመዘን ተገቢ ነው፡፡

በመሆኑም የሴክተር ተቋማት ለዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ ትግበራ መሳካት የበኩላቸውን ሚና መወጣት እንዲችሉ የዕቅድ አፈጻጸማቸውን በመመዘንና ብቃታቸውን በመለየት እውቅና ለመስጠት የሚያስችል ወጥነት ያለው መመዘኛ መመሪያ ማውጣት አስፈልጓል፡፡

ከዚህ አኳያ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣ አዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀጽ 10 (1) (ሠ) አንቀጽ 25 እና ንዑስ አንቀጽ (1) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## አጠቃላይ ሁኔታዎች

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ «የሴክተር ተቋማት ዕቅድ አፈጻጸም ምዘናና ግብረ-መልስ መመሪያ ቁጥር 707/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፦

1) "ሚኒስቴር" ማለት የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ነው፣
2) "ክልል" ማለት በህገ መንግስቱ አንቀጽ 47 መሰረት የተቋቋመ ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ እና የድሬደዋ ከተማ አስተዳደሮችን ይጨምራል፣
3) "የከተማ አስተዳደር" ማለት በህግ ወይም በሚመለከተው መንግስታዊ አካል ውክልና የከተማ አስተዳደር ስልጣንና ተግባር የተሰጠው አካል ነው፣
4) "አብይ ኮሚቴ" ማለት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 የተመለከቱትን አካላት ያለውና ለሚቋቋመው የምዘና የቴክኒክ ኮሚቴ አስፈላጊ የሆኑ ውሳኔዎችን በመስጠት የሚደግፍና የሚያመቻች አካል ነው፣
5) "የቴክኒክ ኮሚቴ" ማለት ምዘናውን በአካል በየክልሉቹና ከተማ አስተዳደሮቹ በመገኘት የሚያከናውኑ ኃላፊዎችንና ባለሙዎችን የያዘ ኮሚቴ ነው፣
6) "ስትራቴጂያዊ አመራር" ማለት የሚኒስቴር መ/ቤቱን የሚኒስትር፣ ሚኒስትር ዴኤታዎች እና በሚኒስትሩ የሚወከል አንድ ግንባር ቀደም አመራር ያካተተ በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ዘርፍ ደረጃ የሚቋቋም ውሳኔ ሰጪ አካል ነው፣
7) "ሴክተር ተቋማት" ማለት በፌዴራል፣ በክልሉች፣ በአዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ከተሞች የሚገኙ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ዘርፍ ተቋማት ማለት ነው፣
8) "የሴክተር ጉባኤ" ማለት በፌዴራል፣በክልሉች፣በአዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ከተሞች የሚገኙ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ዘርፍ ተቋማት መካከል በየዓመቱ ሁለት ጊዜ የሚካሄድ ስብሰባ ነው።

9) "የፌዴራል ተቋማት" ማለት በሚኒስቴር መ/ቤቱ ሥር ተደራጅተው እና የሚኒስቴር መ/ቤቱ ተጠሪ ተቋማት ማለት ነው፣

10) "ምዘና" ማለት የዘርፉ ሴክተር ተቋማትን የማስፈጸም አቅም ግንባታ እና የልማት ሥራዎች ከዕቅድ ክንውን አኳያ መመዘን ማለት ነው፣

11) "ደረጃ" ማለት በዚህ የምዘና መመሪያ መሰረት በምዘናው የሚካተቱ የፌደራል ተቋማትና ክልሎችን የእቅድ አፈጻጸም የሚያሳይ ደረጃ ማለት ነው፣

12) "ግብረ-መልስ" ማለት የሴክተር ተቋማት የዕቅድ አፈጻጸም ምዘና ተካሂዶ የቴክኒክ ቡድኑ በሚያቀርበው ውጤት መሠረት ለተቋማቱ የሚሰጥ ማበረታቻ ወይም የማሻሻያ ድጋፍ ማለት ነው፡፡

## ክፍል ሁለት
## የሴክተር ተቋማት ምዘና

### 3. የምዘናው አስፈላጊነት

የሴክተር ተቋማት የእቅድ አፈጻጸም ምዘና ማካሄድ በሚከተሉት ጉዳዮች ምክንያት አስፈላጊነቱን ያመላክታል፡፡

1) በመላው ሀገሪቱ የሚገኙ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ዘርፍ ተቋማት የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ከማሳካት አኳያ የሚያደርጉትን የሥራ እንቅስቃሴ የአፈጻጸም ደረጃ ለመለካት የሚያስችል በመሆኑ ያመላክታል፡፡
2) በሴክተር ተቋማቱ መካከል ጤናማ የውድድር ስሜት በመፍጠር ለተሻለ አፈጻጸም የሚያነሳሳ በመሆኑ፣ እና
3) በሴክተር ተቋማትን የተሻሉ መልካም ተሞክሮዎች በመለየት ወደ ሌሎች ተቋማት ለማስፋት የሚያስችል በመሆኑ ነው፡፡

### 4. የምዘናው ዓላማ

በሀገር አቀፍ /በብሔር/ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ዘርፍ ተቋማት መካከል በተደረሰበት የጋራ መግባቢያ ሰነድ መሰረት ለበጀት ዓመቱ የተያዘው ዕቅድ በወቅቱ

እየተከናወነ መሆኑን ለመመዘን የወጣ መመሪያ ሲሆን የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች ይኖሩታል፡፡

1) በሀገር አቀፍ ደረጃ የተዘጋጀውን የአምስት ዓመት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በፌዴራል፣ በክልሎችና በአዲስ አበባ እና በድሬደዋ ከተማ አስተዳደሮች በሚገኙ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ዘርፍ ተቋማት ተጣጥሞ መተግበሩን ለማረጋገጥ እና ያለበትን ደረጃ ለመገንዘብ፣
2) በየተቋማቱ በመካሄድ ላይ የሚገኘው የለውጥ ሥራ አመራር ሥራዎች አፈጻጸም በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ እና ከሚጠበቀው ውጤት ጋር ያለውን ያለመጣጣም ክፍተት ለይቶ በማወቅ አስፈላጊውን ፈጣን ድጋፍ ለመስጠት፣
3) የተሻሉ መልካም ተሞክሮዎችን በመለየት ወደ ሌሎች ተቋማት በማሸጋገረ ልማቱን ለማስፋት፣
4) በከተሞች የሚሰጡ አገልግሎቶችን ውጤታማነት ለማረጋገጥ፣
5) የከተሞችን ሃብት በተገቢው ሁኔታ በመጠቀም ወደ ልማት ማንቀሳቀስ መቻሉን ለማረጋገጥ፣
6) የተሻለ አፈጻጸም ያሳዩትን ለማበረታታትና እንቅስቃሴያቸው አጥጋቢ ያልሆኑ ተቋማትን ችግሮችን በመለየት በድጋፍ ለማጠናከር ናቸው፡፡

## 5. የአፈጻጸም ምዘናው የሚከናወንበት ጊዜ

የአፈፃፀም ምዘናው በዓመት ሁለት ጊዜ የሚከናወን ሲሆን የመጀመሪያው ዙር በጥር ወር እንዲሁም የሁለተኛው ዙር ደግሞ ከሐምሌ 2-10/2004 ዓ.ም ይካሄዳል፡፡

## 6. የምዘናው መርህ

1) ጤናማ የሆነ የውድድር ስሜት በሴክተር ተቋማት መካከል መፍጠር፣
2) ለአንድ ዓላማና ለጋራ ውጤት/ስኬት መስራትን ማጎልበት፣
3) የዘርፉን ግቦች በላቀ ደረጃ ለማስፈጸም፣
4) በተቋማት መካከል ቅንጅታዊ አሰራርን ማዳበር፣
5) በተቋማት መካከል ምርጥ ተሞክሮዎችን ማስፋት፡፡

The Federal ... Ministry of Urban ...

## ክፍል ሦስት

## ምዘናውን የሚያካሂዱ አካላት

### 7. ምዘናውን የሚያካሂዱ አካላትን ስለማቋቋም

1) በፖሊሲና ፕሮግራም ዋና አስተባባሪነት

ሀ) ምዘናው በፌዴራል ደረጃ በተማከለ ሁኔታ የሚከናወን ሲሆን አብይ ኮሚቴ እና ሌሎች የምዘና ቡድኖች ይሳተፋሉ፡፡

ለ) ምዘናውን ለማከናወን ከሀገር አቀፍ የከተማ አስተዳደሮች የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ዘርፍ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የተውጣጡ አባላትን የያዘ 14 የምዘና የቴክኒክ ቡድኖች ይዋቀራሉ፡፡

ሐ) የምዘና የቴክኒክ ቡድን 5 አባላት ያሉት እና የተለያየ የሙያ ስብጥር ያላቸው ባለሙያዎችን ያካተተ ይሆናል፡፡

Justify

2) ለምዘና የቴክኒክ ቡድን አባል የሚሆኑ

ሀ) የቴክኒክ አባላት የምልመላ መስፈርት ከሥራው ጋር ተዛማጅ  የሆኑ ሙያዎች ያላቸውን ባለሙያዎች

ለ) ሥራዉን በከፍተኛ ኃላፊነት ስሜት ሊያከናውኑ የሚችሉ

ሐ) ታማኝነት ያላቸው ባለሙያዎች ክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች በጥንቃቄ መልምለው ለሚያስተባብረው የፌዴራል መ/ቤት ይልካሉ፡፡

### 8. የአብይ ኮሚቴው አባላት ዝርዝር

1) የከተማ ልማት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ............................... ሰብሳቢ
2) የፖሊሲና ፕሮግራም ቢሮ ኃላፊ ...................................... ጸሐፊ
3) የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማትና ሬጉላቶሬ ቢሮ ኃላፊ ....... አባል
4) የማስፈጸም አቅም ግንባታና የለውጥ ሥራ አመራር ቢሮ ....... አባል
5) የከተሞች መልካም አስተዳደርና አቅም ግንባታ ቢሮ ኃላፊ ኃላፊ...አባል
6) የሚኒስቴሩ ጽ/ቤትና የሚኒ ካቢኔ ጉዳዮች ቢሮ ኃላፊ ...............አባል
7) የድጋፍ ሰጪ ማስተባበሪያ ቢሮ ኃላፊ ...................................አባል
8) የሕዝብ ግንኙነትና ኮሚዩኒኬሽን ጽ/ቤት ኃላፊ.........................አባል

9) የመኖሪያ ቤቶች ልማትና የመንግስት ህ/ ክ/ ቢሮ ኃላፊ …… አባል

10) የመሬት ልማት ማኔጅመንት ቢሮ ኃላፊ……………………… አባል

11) የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፐራይዞች ልማት ኤጀንሲ ኃላፊ……አባል ይሆናሉ።

## 9. የአብይ ኮሚቴው ተግባር እና ኃላፊነት

1) የምዘና ሂደቱን በበላይነት ይመራል፣
2) ለምዘናው የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን እንዲሟሉ ያደርጋል፣
3) ለምዘናው ሂደት መቀላጠፍ አስፈላጊ ውሳኔዎችን ያስተላልፋል፣
4) የሴክተር ተቋማትን ውጤት መርምሮ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ስትራቴጂያዊ አመራር አቅርቦ ያጸድቃል፣
5) ለሴክተር ተቋማት እንደአፈጻጸማቸው የሚሰጡ ግብረ-መልሶችን የውሳኔ ሃሳብ ስትራቴጂያዊ አመራር አቅርቦ ያጸድቃል።

## 10. የፖሊሲና ፕሮግራም ቢሮ ተግባር እና ኃላፊነት

1) የዓብይ ኮሚቴውን ስራዎች ያስተባብራል ያስፈፅማል
2) የምዘና የቴክኒክ ቡድኑን ይመሰምላል፣
3) ለቴክኒክ ቡድኑ የእርስ በርስ ትውውቅ ፕሮግራም በማዘጋጀት ስለምዘናው ሂደት ስልጠና ይሰጣል፣ ቡድኖቹን ወደሚመደቡበት ተቋም ያሠማራል፣
4) ምዘናው የደረሰበትን ደረጃ ይከታተላል፤ ለቴክኒክ ቡድኑ ድጋፍ ያደርጋል፣
5) በምዘናው ወቅት ሊሚያጋጥሙ የመንግስት መመሪያዎች የአፈፃፀም ችግሮች ላይ የመፍትሔ አስተያየት ለዓብይ ኮሚቴው ያቀርባል ያስቀምጣል፣
6) የሴክተር ተቋማቱን የዕቅድ አፈጻጸም ምዘና ውጤት ከቴክኒክ ቡድኖቹ በመሰብሰብ እና በማጠናቀር በተቋማቱ መካከል የተገኘውን የአፈጻጸም ምዘና ውጤት እና ደረጃ ለአብይ ኮሚቴ ያቀርባል፣ እና
7) የሴክተር ተቋማትን የምዘና ውጤት እና ግብረ-መልስ የያዘ ሪፖርት በሚዘጋጅ ለሴክተር ጉባኤ መድረክ ያቀርባል።

## 11. የምዘና የቴክኒክ ቡድን አወቃቀር

1) የምዘና ቴክኒክ ቡድኑ ከፌዴራል፣ ከክልሎች፣ ከአዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮች ከሚገኙ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ዘርፍ ተቋማት የሚውጣጡ ኃላፊዎችንና ባለሙያዎችን የያዘ ሲሆን 14 የሚገኙባቸው ቡድኖች የቴክኒክ ኮሚቴዎች ይዋቀራሉ።

2) የምዘናው ቴክኒክ ቡድን ከፌዴራል፣ ከክልሎች እና ከከተማ አስተዳደሮች የተሰባሰቡ ባለሙዎች የተለያየ የሙያ ስብጥር እንዲኖራቸው ተደርጎ ይዋቀራል።

3) የምዘናው ቴክኒክ ቡድን ከፌዴራል በተውጣጡ ባለሙያዎች የሚመራ ይሆናል።

## 12. የምዘና የቴክኒክ ቡድኑ ተግባርና ኃላፊነት

1) የምዘና ቴክኒክ ቡድኑን በተመለከተ የሚሠጡ መግለጫዎችንና ሥልጠናዎችን ይከታተላል፣

2) የሥራ እቅድና የቡድን የሥነ-ምግባር መመሪያ ያዘጋጃል፣ ሥራውን በእቅድ ያከናውናል፣ ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶችን ይረከባል፣ በንዑሳን ቡድን በመደራጀት ምዘና በሚካሄድበት ተቋም በመገኘት የምዘና ሂደቱን አስመልክቶ ግንዛቤ ይፈጥራል፣ ምዘናውን ያከናውናል፣

3) የቴክኒክ ቡድኑ በየዕለቱ በተመደበበት ቦታ በሰዓቱ በመገኘት ምዘናውን በማካሄድ እና በመፈራረም መረጃዎችን በአግባቡ ይይዛል፣

4) ከቸልተኝነት ነጻ በሆነና በመልካም ሥነ-ምግባር ምዘናውን በጥራት ያከናውናል፣

5) በመመሪያው ላይ የተቀመጠውን የአሰራር ስልት በአግባቡ ይተገብራል፣

6) ከፖሊሲና ፕሮግራም ቢሮ የሚሰጠውን ተግባር ያከናውናል።

7) የስነ-ምግባር ደንብ ያዘጋጃል

8) የተካሄደውን ምዘና በየዕለቱ ሞልቶ በፊርማው ያረጋግጣል፣

9) የምዘናውን ማጠቃለያ የቃል ግብ-መልስ ለየተቋማቱ ያስራጫል እንደዚሁም የሪፖርቱን ኮፒ ይልካል።

## ክፍል አራት

## የምዘናው አካሄድ እና ነጥብ አሰጣጥ

### 13. የምዘናው አካሄድ እና አገላለጽ

#### 1) የምዘናው አካሄድ

ሀ) ማንኛውም የምዘና ቴክኒክ ቡድን በተመደቡበት ተቋም በመገኘት የምዘናውን በማካሄድ በየዕለቱ ያገኘውን ውጤት ይሞላል፣

ለ) የምዘና ቴክኒክ ቡድኖች አባላት ውጤት የሴክተር ተቋማቱ አማካይ ውጤት ተደርጎ ይወሰዳል፣

ሐ) የምዘና ቴክኒክ ቡድኖች በተመደቡበት ክልል/ከተማ አስተዳደር ምዘና ሲያጠናቅቁ ውጤቱን በማጠቃለል ከመግለጫና ዝርዝር መረጃዎች ጋር በወቅቱ ለፖሊሲና ፕሮግራም ቢሮ ሪፖርት ያርባሉ፣

መ) የምዘና ቴክኒክ ቡድኖች አጠቃላይ ሪፖርት በሚኒስቴር መ/ቤቱ ለዚሁ ተግባር ለተቋቋመው አብይ ኮሚቴ ቀርቦ ከተመረመረ በኋላ ይጸድቃል፣

#### 2) የምዘናው አገላለጽ

ሀ) ባለሙያዎቹ የምዘና ሪፖርቱን አዘጋጅተው በማጠናቀቅ ለፖሊሲና ፕሮግራም ቢሮ ያቀርባሉ፣

ለ) ፖሊሲና ፕሮግራም ቢሮ ሪፖርቱን ለአብይ ኮሚቴው አቅርቦ አስተያየት እንዲሰጥበት ያደርጋል፣

ሐ) የአብይ ኮሚቴው አስተያየት በሪፖርት ተካቶ ከዳበረ በኋላ ለክልሎች ተልኮ አስተያየታቸውን በ3 ቀናት ውስጥ እንዲሰጡ ይደረጋል፣

መ) በመጨረሻው የክልሎች አስተያየት በሪፖርቱ ተካቶ ለአብይ ኮሚቴው ቀርቦ እንዲጸድቅ ይደረጋል፣

ሠ) በመጨረሻው የፀደቀው በፖርት ለሴክተር ጉባኤ ተዘጋጅቶ ቀርቦ በምዘና መስፈርቱ መሠረት የተመዘኑትን ተቋማት አፈጻጸማቸው ጠንካራ ሆኖ ከተገኘ አዎንታዊ (Positive Response) ድክመት የታየ ከሆነ ድጋፋዊ ወይም ማሻሻያ (Supportive or corrective Response) ግብረ-መልስ ይሰጣል።

ረ) የመጨረሻውን ቅርጽ የያዘው የምዘና ሪፖርት ለሚመለከታቸው አካላት ይሰራጫል።

## 14. የምዘናው ግብአቶች

በምዘናው ሂደት እንደመነሻ የሚወሰዱ የማገናዘቢያ ሠነዶች፡-

1) በበጀት ዓመቱ ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ጋር የተፈረመ የጋራ መግባቢያ ሠነድ (የበጀት አመቱ ዕቅድ)፣
2) የየተቋማቱ የበጀት አመት የ6 ወራት ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት፣ ዓመታዊ ሪፖርት፣ እና
3) እንዲሁም ሌሎች ከሥራው ጋር የተያያዙ መረጃዎች ናቸው።

## 15. የምዘናው ስልት

ምዘናውን ለማካሄድ የሚከተሉትን የምዘና ስልቶችን መከተል ተገቢ ይሆናል፡-

1) የሚመለከታቸውን የሥራ ኃላፊዎች ማነጋገር፤
2) ከሥራው ጋር ተያያዥ የሆኑ ሠነዶችን መመልከት (የአሰራር መሪያዎች፣ የጋራ መግባቢያ ሰነድ፣ የእቅድ አፈጻጸም ሪፖርቶች፣ ቃለ-ጉባኤዎችን ወዘተ...)፣
3) የመስክ ምልከታዎችን ማካሄድ፤
4) የተቋማቱን ተገልጋይ/ተጠቃሚ ማነጋገር፣
5) ተቋሙ እቅዱን ለመፈጸም ያደረገው ጥረትና የተጠቀመበት አማራጭ የአሰራር ስልት፣
6) በየዕለቱ ነጥብ በመስጠትና በመፈራረም የየተቋማቱን ሪፖርት ማጠናቀር፣
7) ለየተቋማቱ የማጠቃለያ አስተያቶችን መስጠት፣
8) በየተቋማቱ የታዩ ጠንካራና ደካማ ጎኖችን ጨምቆ ማውጣትና ውጤቶቹን ለቡድን መሪው መስጠት፣ እና
9) የተሻለ አፈጻጸም የታየባቸውን ተቋማት በመለየት የተሻሉበትን ሥራና የተሻለ ሥራ የተከናወነበትን ምክንያት ለይቶ ምርጥ ተሞክሮ መቀመር ይሆናል።

## 16. የምዘናው ነጥብ አሰጣጥ

1) ከላይ በአንቀጽ 13 በተጠቀሱት የምዘና ስልቶችና ከዚህ መመሪያ ጋር በአባሪነት በተያያዘው መገምገሚያ ቼክሊስት መሠረት ይፈጸማል፣

2) ምዘናው በተመረጡ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ግቦችና ተግባራት ላይ ያተኩራል፤

3) የዘርፉ የልማት ሥራዎች ካላቸው ትኩረት አኳያ እያንዳንዳቸው ክብደት የሚኖራቸው ይሆናል፣ በዚሁ መሠረት፡-

ሀ) የሥራ ዕድል ፈጠራ ሥራዎች ............................ 25%

ለ) የመሬት ልማትና ማኔጅመንት ሥራዎች.................. 15%

ሐ) የመኖሪያ ቤቶች ልማት ሥራዎች............................15%

መ) የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማት ሥራዎች................10%

ሠ) የመልካም አስተዳደርና አቅም ግንባታ ሥራዎች...........10%

ረ) የከተማ ፕላን፣ ጽዳትና ውበት ሥራዎች......................10%

ሰ) የዕቅድ ዝግጅት፣ አፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ሥራዎች....5%

ሸ) የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂና ዳታቤዝ ልማት ሥራዎች...... 5%

ቀ) የማስፈጸም አቅም ግንባታና የለውጥ ስራዎች............... 5%

ክብደት የሚኖራቸው ይሆናል።

በ) በክልሎች እና የከተማ አስተዳደሮች የሚገኙ ተቋም የምዘና ውጤት ከ100 ከተሰላ በኃላ በተራ ቁጥር 14.8 በተሰጠው የሥራዎቹ ክብደት መሰረት ተባዝቶ አጠቃላይ የክልሎች እና የከተማ አስተዳደሮች ውጤት ይሆናል።

ተ) የክልልና የአዲስ አበባ እና የድሬደዋ ከተማ አስተዳደሮች የሚገኙ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ዘርፍ ተቋማት የምዘና ሂደት ነጥብ አሰጣጥ፡-

ቸ) የሴክተር ተቋሙ ዕቅድ አፈጻጸም ድምር ውጤት ወደ 80% ይቀየራል፤

ኀ) ቀሪው 20% በፌዴራል ደረጃ የሚገኘው ተመሳሳይ (አቻ) ተቋም የሚሰጡት ውጤት ከ20% የሚሞላ ሲሆን ውጤቱ በተቋሙ ሥራ አመራር ኮሚቴ ጸድቆ ለፖሊሲና ፕሮግራም ቢሮ በወቅቱ ይተላለፋል።

## 17. የፌዴራል ተቋማት ነጥብ አሰጣጥ፡-

1) የተቋሙ ዕቅድ አፈጻጸም ውጤት ከ100% ከተሞላ በኋላ ወደ 50% ይቀየራል፣
2) የተቋማቱ የማስፈጸም አቅም ግንባታና የለውጥ ሥራዎች የምዘና ውጤት በማስፈጸም አቅም ግንባታና የለውጥ ሥራ አመራር ቢሮ ተመዝኖ ከ10% ይሞላል፣
3) የቢሮዎች የ6 ወር የGTP መድረክ አፈጻጸም ምዘና ውጤት ተወስዶ ወደ 10% ከተለወጠ በኋላ በፖሊሲና ፕሮግራም ቢሮ የሚሞላ ሲሆን፣
4) ቀሪው 30% የክልል አቻ ተቋማት አማካይ ውጤት ተወስዶ የሚደመር ይሆናል፡፡
5) በአጠቃላይ ከ16.6.1 — 16.6.4 የተሞላው ተደምሮ አጠቃላይ የተቋሙ ውጤት ከ100% ይሆናል፡፡
6) በክልልና ከተማ አስተዳደሮች ግልጽ መዋቅር ያልተዘረጋላቸው የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ፣ የተገጣጣሚ ህንጻ አካላት ማምረቻ ድርጅት እና የድጋፍ ሰጪ ማስተባበሪያ ቢሮ ነጥብ አሰጣጥ በተራ ቁጥር 16.5.1 የተሰጠው ነጥብ ከ80% ሆኖ ቀሪው 20% በፖሊሲና ፕሮግራም ቢሮ የሚሞላ ይሆናል፡፡

## 18. የሴክተር ተቋማት ምድብ

የዕቅድ አፈጻጸም ምዘናው በክልሎች እና በአዲስ አበባና ድሬደዋ ከተማ አስተዳደሮች በሚገኙ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ዘርፍ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት በሁለት ምድብ ተከፍለው በክልል ደረጃ የሚወዳደሩ ሲሆን የፌዴራል ተቋማትም በሁለት ምድብ ተከፍለው በፌዴራል ተቋማት መካከል ባስገኙት አፈጻጸም መሰረት በመወዳደር የምዘና ውጤትና ደረጃ የሚወጣ ይሆናል፡፡ ምድቦቹም፡-

1) የክልሎች፣ የአዲስ አበባ እና የድሬደዋ ከተማ አስተዳደሮች የምዘናምድብ

ምድብ አንድ

ሀ) በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት
ለ) በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት
ሐ) በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት
መ) በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

ሠ) በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እና

ረ) በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የሚገኙ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽንዘርፍ ተቋማት አንድ ላይ የሚወዳደሩ ይሆናል፡፡

ምድብ ሁለት

ሀ) በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

ለ) በሶማሊ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

ሐ) በቤንሻንጉል ጉሙዝ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

መ) በጋምቤላ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት እና

ሠ) ሐረሪ ህዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የሚገኙ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ዘርፍ ተቋማት አንድ ላይ የሚወዳደሩ ይሆናል፡፡

2) የፌዴራል ተቋማት የምዘና ምድብ

ምድብ አንድ

ሀ) የማስፈጸም አቅም ግንባታና የለውጥ ሥራ አመራር ቢሮ

ለ) የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ

ሐ) የከተማ መሬት ልማትና ማኔጅመንት ቢሮ

መ) የተቀናጀ የመሬት ልማትና መሬት ነክ የመረጃ ሥርዓት ፕሮጀክት ጽ/ቤት

ሠ) የከተማ መሬትና መሬት ነክ ቋሚ ንብረት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ

ረ) የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማትና ሬጉላቶሪ ቢሮ

ሰ) የመኖሪያ ቤቶች ልማትና የመንግሥት ህንጻዎች ኮንስትራክሽን ቢሮ

ሸ) የከተሞች መልካም አስተዳደርና አቅም ግንባታ ቢሮ

ቀ) የከተማ ፕላን፣ ዕዳትና ውበት ቢሮ

በ) የፖሊሲና ፕሮግራም ቢሮ

ተ) የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂና ዳታ ቤዝ ልማት ቢሮ

ምድብ ሁለት

ሀ) የድጋፍ ሰጪ ማስተባበሪያ ቢሮ

ለ) የመንግሥት ቤቶች ኤጀንሲ እና

ሐ) የተገጣጣሚ ሕንፃ አካላት ማምረቻ ድርጅት የሚገኙ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ዘርፍ ተቋማት አንድ ላይ የሚወዳደሩ ይሆናል።

## ክፍል አምስት

## ምዘና የሚካሄድባቸው የሴክተር ተቋማት

19. አፈጻጸማቸው የሚመዘነው በፌዴራል፣ በክልል እና በአዲስ አበባና ድሬደዋ ከተማ አስተዳደሮች የሚገኙ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ዘርፍ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ።

1) በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት
   - ሀ) ንግድ፣ ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮ
   - ለ) የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ልማት ኤጀንሲ
   - ሐ) የከተማ ፕላን ዝግጅት፣ ክትትልና ግምገማ ዋና የሥራ ሂደት
   - መ) መሬት የማልማትና መረጃ መስጠት ዋና የሥራ ሂደት
   - ሠ) የመሰረተ ልማት ማስፋፊያ ሥራዎች
   - ረ) ጽዳትና ውበት ዋና ሥራ ሂደት
   - ሰ) ኮንስትራክሽን፣መንገድ ትራንስፖርት ቢሮ
   - ሸ) የኮንስትራክሽን ሪጉሌሽንና ፍቃድ ምዝገባ የስራ ሂደት
   - ቀ) የቤቶች ልማት ኤጀንሲ
   - በ) የህንጻ ዲዛይንና ኮንስትራክሽን የስራ ሂደት

2) በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት
   - ሀ) የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ቢሮ
   - ለ) የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ
   - ሐ) የመሬት ልማትና ይዞታ አስተዳደር ዋና የሥራ ሂደት
   - መ) የከተማ ኘላን፣ ጽዳትና ውበት ዋና የሥራ ሂደት
   - ሠ) የከተሞች መልካም አስተዳደርና አቅም ግንባታ ዋና የሥራ ሂደት
   - ረ) የመኖሪያ ቤቶች ልማትና የመንግስት ህንጻዎች ኮንስትራክሽን ዋና የሥራ ሂደት
   - ሰ) የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ሬጉላቶሪና አቅም ግንባታ የሥራ ሂደት

ሸ) የጥናት፣ ዕቅድና በጀት ዝግጅት ደጋፊ የሥራ ሂደት

ቀ) የኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ደጋፊ የሥራ ሂደት

3) <u>በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮ</u>

ሀ) የጥቃቅንና አነስተኛ ንግድ ሥራዎች ኢንተርፕራይዝ ኢጀንሲ

ለ) የከተማ ፕላን ኢንስቲትዩት

ሐ) የከተማ ፕላን አፈጻጸም፣ ጽዳትና ውበት ሥርዓት ማሻሻያ ዋና የሥራ ሂደት

መ) የከተማ መሬት ልማትና ማኔጅመንት ዋና የሥራ ሂደት

ሠ) የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ሬጉላቶሪና አቅም ግንባታ ዋና የሥራ ሂደት

ረ) የዲዛን ኮንስትራክሽን ዋና የስራ ሂደት

ሰ) የኮንስትራክሽንና ቤቶች ልማት ኤጀንሲ

ሸ) የከተሞች መልካም አስተዳደርና አቅም ግንባታ ዋና የሥራ ሂደት

ቀ) የዕቅድ ዝግጅት፣ አፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ደጋፊ የሥራ ሂደት

4) <u>በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የከተማ ልማትና ኮንትራክሽን ቢሮ</u>

ሀ) የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ልማት ኤጀንሲ

ለ) የቤቶች ልማት ማስተላለፍና ማስተዳደር የሥራ ሂደት

ሐ) የከተማ ፕላን የአፈጻጸም ክትትል እና የጽዳትና ውበት የሥራ ሂደት

መ) የከተማ መሬት ልማትና ማኔጀመንት የሥራ ሂደት

ሠ) የከተሞች አደረጃጀትና ያልተማከለ አስተዳደር የሥራ ሂደት

ረ) የከተማ መሠረተ ልማትና የሕዝብ ተሳትፎ የሥራ ሂደት

ሰ) የከተሞች የሰው ኃይል ልማትና የድጋፍ አሰጣጥ የሥራ ሂደት

ሸ) የኢንዱስትሪ ልማት እና የአቅም ግንባታ ማስፋፊያ ዋና የሥራ ሂደት

ቀ) የዲዛይን ቁጥጥርና ማረጋገጥ የሥራ ሂደት

በ) የኮንትራት ቁጥጥር፣ ምዝገባና አስተዳደር የሥራ ሂደት

ተ) የሬጉሌሽን፣ ኢንስፔክሽንና የግንባታ ዕቃዎች ቴክኖሎጂ ጥናት ዋና የሥራ ሂደት

ቸ) የዕቅድና በጀት ዝግጅት ክትትልና ግምገማ የሥራ ሂደት

ኀ) የኢንፎርሜሽንና ቴክኖሎጂ እና ዳታቤዝ ልማት የሥራ ሂደት

5) በሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በከተማ ልማት፣ኮንስትራክሽንና ኢንዱስተሪ ቢሮ

ሀ) የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ

ለ) የከተማ መልካም አስተዳደርና አቅም ግንባታ የሥራ ሂደት (የመስረተ ልማት ሥራዎች)

ሐ) የመኖሪያ ቤቶች ልማት እና የመንግስት ህንጻዎች ግንባታ (ቤቶች ልማት አስተዳደር)

መ) የኮንስትራክሽን፣ የውል አስተዳደር እና የዲዛይን ሱፐርቪዥን የሥራ ሂደት

ሠ) የከተማ መሬት ልማትና ማኔጅመንት የሥራ ሂደት

ረ) የከተማ ፕላን፣ ጽዳትና ውበት ማሻሻያ የሥራ ሂደት

ሰ) የፖሊሲ፣ ፕሮግራም፣ እቅድ ዝግጅት እና አፈጻጸም ክትትል እና ግምገማ የሥራ ሂደት

6) በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ንግድ፣ ንዱስትሪ፣ትራንስፖርትና ከተማ ልማት ቢሮ

ሀ) የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይ ልማት ኤጀንሲ

ለ) የከተማ ፕላን ጽዳትና ውበት የሥራ ሂደት

ሐ) የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪና ሬጉላቶሪ የሥራ ሂደት

መ) የመኖሪያ ቤቶች ልማትና የመንግሥት ህንጻዎች ኮንስትራክሽን የሥራ ሂደት

ሠ) የከተማ መሬት ልማት የሥራ ሂደት

ረ) የከተሞች መልካም አስተዳደርና አቅም ግንባታ የሥራ ሂደት

ሰ) የዕቅድ ዝግጅት ክትትልና ግምገማ የሥራ ሂደት

7) በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት የንግድ፣ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮ

ሀ) የኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ

ለ) የከተሞች አደረጃጀት፣ ፕላን ዝግጅትና ክትትል ዋና የሥራ ሂደት

ሐ) የመሬት ልማትና አስተዳደር ዋና የሥራ ሂደት

መ) የከተማ መሬትና መሬት ነክ መረጃ ዝግጅት አስተዳደርና አቅርቦት የሥራ ሂደት

ሠ) የቤቶች ልማትና አስተዳደር ዋና የሥራ ሂደት

ረ) የመሰረተ ልማት አቅርቦትና አስተዳደር ዋና የሥራ ሂደት

ሰ) የከተሞች ፅዳት፣ ውበት ልማትና መናፈሻ አገልግሎት የሥራ ሂደት

ሸ) የዲዛይንና ግንባታ ቁጥጥር ባለስልጣን

8) <u>በጋምቤላ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ቢሮ</u>

ሀ) ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ

ለ) የከተማ መሬት ልማትና ማኔጀጅመንት ስራ ሂደት

ሐ) የኮንስትራክሽን ዲዛይን፣ ግንባታ ቁጥጥርና አስተዳደር የሥራ ሂደት

መ) የመኖሪያ ቤቶች ልማትና የመንግሥት ህንጻዎች ኮንስትራክሽን ዋና ሥራ ሂደት

ሠ) የከተማ ፕላን፣ ጽዳትና ውበት ዋና የሥራ ሂደት

ረ) የከተሞች አደረጃጀት፣ መልካም አስተዳደርና አቅም ግንባታ የሥራ ሂደት

ሰ) የፖሊሲ፣ ፕሮግራም እና ዕቅድ ዝ/ክ/ና ግምገማ የሥራ ሂደት

ሸ) የኢንፎርሜሽንና ኮሚ/ቴክ/ልማት የሥራ ሂደት

9) <u>በሐረሪ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ቢሮ</u>

ሀ) የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ

ለ) የከተማ ኘላን የሥራ ሂደት

ሐ) የመኖሪያ ቤቶች ልማትና ኮንስትራክሽን ሬጉላቶሪ ኤጀንሲ

መ) የዲዛይን ዝግጅት፣ ኮንስትራክሽን አስተዳደርና ግንባታ ቁጥጥር የሥራ ሂደት

ሠ) የመሬት ልማት ማኔጅመንት ባለሥልጣን

ረ) የፖሊሲ መረጃ ጥናት የሥራ ሂደት

10) <u>የሥራ እስኪያጅ ጽ/ቤት</u>

ሀ) የከተሞች መልካም አስተዳደር (መሠረተ ልማት) የሥራ ሂደት

ለ) የጽዳትና ውበት የሥራ ሂደት

11) <u>በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሥራ አስከያጅ ጽ/ቤት ሥር፡-</u>

ሀ) ከተማ ፕላንና መረጃ ኢንስቲትዩት

ለ) የመሬት ልማት ባንክና ከተማ ማደስ ፕሮጀክት ጽ/ቤት

ሐ) የይዞታ አስተዳደር ሽግግር ጊዜ መስተንግዶ ፕሮጀክት ጽ/ቤት

መ) ግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን

ሠ) የተቀናጀ የመሬትና መሬት ነክ መ/ስ/ዝ/ፕ/ማስተባበሪያ ጽ/ቤት

ረ) የማይንቀሳቀስ ንብረት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ

ሰ) የደረቅ ቆሻሻ መልሶ መጠቀምና ማስወገድ ፕሮጀክት ጽ/ቤት

ሸ) የውበት፣ መናፈሻና ዘላቂ ማረፊያ ልማት ኤጀንሲ

ቀ) የጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ

በ) የውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን

ተ) የእሳትና ድንገተኛ አደጋዎች መከላከልና መቆጣሪያ ኤጀንሲ

12) <u>በኮንስትራክሽንና ቤቶች ልማት ቢሮ</u>

ሀ) የቤቶች ልማት ፕሮጀክት ጽ/ቤት

ለ) የቤቶች አስተዳር ኤጀንሲ

ሐ) የህብረተሰብ ተሳትፎ ልማት ኤጀንሲ

መ) የመንግስት ኮንስትራክሽን ኤጀንሲ

ሠ) የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማት ቁጥጥር ባለስልጣን

ረ) የኮብልስቶን ማስተባበሪያ ጽ/ቤት

ሰ) የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ልማት ኤጀንሲ

13) <u>በድሬደዋ ከተማ አስተዳደር</u>

ሀ) የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ

ለ) የመሬት ልማት ባለሥልጣን

ሐ) የቤቶች ልማት ፕሮጀክት ጽ/ቤት

መ) ኮንስትራክሽንና ኢንዱስትሪ ሬጉላቶሪና አቅም ግንባታ አብይ የሥራ ሂደት

ሠ) የመሰረተ ልማት ዩኒት (ULGDP)

ረ) ፅዳትና ውበት ኤጀንሲ

ሰ) የፕላንና ፕሮግራም አገልግሎት የሥራ ሂደት

ሸ) የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂና ዳታቤዝ ልማት

14) <u>በፌዴራል ደረጃ የሚገኙ ሴክተር ተቋማት ቡድን አንድ</u>

ሀ) የማስፈጸም አቅም ግንባታና የለውጥ ሥራ አመራር ቢሮ

ለ) የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ

ሐ) የከተማ መሬት ልማትና ማኔጅመንት ቢሮ

መ) የተቀናጀ የመሬትና መሬት ነክ መረጃ ሥርዓት ዝርጋታ ሮጀክት

ሠ) የከተማ መሬትና መሬት ነክ ቋሚ ንብረት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ

ረ) የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማትና ሬጉላቶሪ ቢሮ

ሰ) የመኖሪያ ቤቶች ልማትና የመንግሥት ህንጻዎች ኮንስትራክሽን ቢሮ

ቡድን ሁለት

ሀ) የከተሞች መልካም አስተዳደርና አቅም ግንባታ ቢሮ

ለ) የከተማ ፕላን፣ ፅዳትና ውበት ቢሮ

ሐ) የፖሊሲና ፕሮግራም ቢሮ

መ) የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂና ዳታ ቤዝ ልማት ቢሮ

ሠ) የድጋፍ ሰጪ ማስተባበሪያ ቢሮ

ረ) የመንግሥት ቤቶች ኤጀንሲ

ሰ) የተገጣጣሚ ሕንፃ አካላት ማምረቻ ድርጅት

## ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

20. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

በዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች ጋር እስካለተቃረኑ ድረስ አግባብነት ያላቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የክትትል፣ ግምገማና ግብረ-መልስ የአሰራር ማኑዋሎች በዚህ መመሪያ ባልተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ እንዲሁም ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም በማሟያነት ተፈፃሚ ይሆናሉ።

21. የመመሪያው ተፈጻሚነት

ይህ መመሪያ በፌደራል፣ በክልል እና አዲስ አበባና ድሬደዋ ከተማ አስተዳደሮች የሚገኙ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ዘርፍ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል ።

## 22. መመሪያውን ስለማሻሻል

ይህ መመሪያ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማንኛውም ጊዜ ሊሻሻል ይችላል፡፡

## 23. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚ/ር ስትራቴጂያዊ አመራር ቀርቦ ከፀደቀበት ሰኔ 2004 ጀምሮ ተግባራዊ ይሆናል፡፡

መኩሪያ ኃይሌ

የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ሚኒስትር

2004 ዓ.ም

አባሪ 01፡ በምዘናው የሚካተቱ ተቋማት መመዘኛ ቼክ-ሊስት

የ.........................................ክልል የ................በጀት አመት

የ.................... ዙር የዕቅድ አፈፃፀም መመዘኛ ቼክ ሊስት

| ተ.ቁ | የታቀዱ ግቦችና ተግባራት | መለኪያ | የ6 ወር ዕቅድ | ክንውን | ለስራው የተሰጠ ክብደት ከመቶ | በአፈጻጸም የተገኘ ነጥብ ከመቶ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| I | | | | | | |
| 1 | | | | | | |
| 2 | | | | | | |
| 3 | | | | | | |

የምዘና የቴክኒክ ቡድኑ አስተያየት ------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------

---------------------------

| ተ.ቁ | ሥም | የስራ ድርሻ | ፊርማ | ቀን |
|---|---|---|---|---|
| 1. | ------------------------------ | -------------------- | --------------- | -------------- |
| 2. | ------------------------------ | -------------------- | --------------- | -------------- |
| 3. | ------------------------------ | -------------------- | --------------- | -------------- |
| 4. | ------------------------------ | -------------------- | --------------- | -------------- |
| 5. | ------------------------------ | -------------------- | --------------- | -------------- |

የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ሚኒስትር አስተያየትና ውሳኔ------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------